ኣስፈላጊ መረጃ ስለ፡

# የ7ኛ ክፍል ክትባቶች

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

ወሊንግቶን-ዱፈሪን- ጋልፍ
ጤናዎ የተጠበቀ ይሁን

ውድ ወላጅ ወይ ሞግዚት፡

ወሊንግቶን-ዱፈሪን-ጋልፍ የህብረተሰብ ጤና ክፍል፡ ለ ኣሁን እና ለቀጣይ ግዜ የሚከላከሉላቸው ሶስት ኣስፈላጊ በነጻ የሚሰጡ ክትባቶች ለመስጠት ወደ ልጆት ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። የህብረተሰብ ጤና ነርሶች በዚ ታች በተገለጸው ቦታ በተጠቀሰው ቀን ይገኛሉ፡

## [SCHOOL NAME] በ [DATE]

እነዚ ክትባቶች ኣስተማማኝ እና ውጤታማ ናቸው፡ ከ ከባድ በሽታዎችም ይከላከላሉ። የልጆት እና የህብረተሰባችን ጤና ለመጠበቅ ክትባቱን ለመውሰድ ፍቃድዎን እንዲሰጡን ኣጥብቀን እንጠይቃለን።

## የሚሰጡ ክትባቶች

### 1 መኒንጎኮካል

ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት-ኤሲዋይዳብሊው ከ ማጅራት ገትር በሽታ ይከላከላል፡ ይሄ በሽታ ኣንጎልና የጀርባ ኣጥንትን ሊጎዳ ከሚችል ከባድ ኢንፈክሽን ይከላከላል። ይሄ በቀላሉ የሚተላለፍ እና ለሂወት ኣስጊ ነው።

ይሄ ክትባት ከ ኣራት የተለመዱ የ ኤ፡ ሲ፡ ዋይ፡ እና ዳብሊው135 በሽታ ዓይነቶች ይከላከላል።

### 2 የጉበት በሽታ ‘ቢ’

ይሄ ክትባት በ ጉበት በሽታ ‘ቢ’ ቫይረስ የሚመጡ የ ጉበት ካንሰር እና የጉበት በሽታዎች ይከላከላል።
ኣብዛኛው ግዜ ይህ ክትባት ለ ጉዞ፡ ለከፍተኛ ትምህርት፡ እና ለኣንዳንድ ስራዎች ኣስፈላጊ ነው።

### 3 ኤችፒቪ

ክትባት ኤችፒቪ-9 ከ ጭንቅላት፡ ኣንገት እና የብልት ካንሰሮች እንዲሁም ኪንታሮት ይጠብቃል።

ከ ዘጠኝ የተለመዱ የ ኤችፒቪ ኣይነቶች ይጠብቃል። ብዙ ሰዎች በሂወት ዘመናቸው ኣንዴ ከ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ጋር ንክኪ ይኖራቸዋል።

## ምን ማድረግ ያስፈልጋችዋል

ለ ልጆት፡ በኦንላይን የሚሞላ የፍቃድ ቅጹን፡ በተቻለ መጠን በፍጥነት ይሙሉት። ይህ የህብረተሰብ ነርሶቹ፡ ልጆቻቹ ክትባቱን መውሰድ የሚችሉ ከሆነ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

ልጆቻቹ ከዚ በፊት ከክትባቶቹ መሃል የወሰዱት ክትባት ካለ፡ ቅጹ ላይ መጻፍ ትችላላቹ።

**ፍቃድ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ**

## ተጨማሪ መረጃ: በቋንቋዎ

ታች በብዙ ቋንቋዎች የተቀመጡ የመረጃ ገጾች በማየት ስለ እያንዳንዱ ክትባት ይማሩ።

- ኢንግሊዘኛ
- français (ፈረንሳይኛ)
- አማርኛ
- عربي (ዓረብ)
- درى (ዳሪ)
- हिन्दी (ህንድ)
- नेपाली (ኔፓል)
- español (ስጳኛ)
- ታታሎግ
- ትግርኛ
- TiếngViệt (ቬትናሜዝ)

ጥያቄ ካሎት ወይም የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት እርዳታ ካስፈለጎት በዚ ቁጥር ይደውሉ 1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር. 7006 በዚ ቁጥር ከደወሉ የህብረተሰብ ነርስን ማናገር ይችላሉ፡ ወይም በዚ ይግቡ wdgpublichealth.ca/immunizegr7.

የልጆቻቹን እና የህብረተሰባችን ጤና ለመጠበቅ ስለተባበሩን እናመሰግናለን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር,



**ዶር. ማቲው ተነንባኦም፡ ሓኪም፡ ሲሲኤፍፒ፡ ኤምፒኤች፡ ኤፍኣርሲፒሲ**

**ተባባሪ የህክምና ጤና ቢሮ ሓላፊ**

---

## ልጆቻቹ በክትባት ቀን ምቹነት እንዲሰማቸው መርዳት

የህብረተሰብ ጤና ክፍል ልጆቻቹ ስለ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወሰዱ ክትባት በተመለከተ የሚኖራቸው ተሞኩሮ በተቻለ መጠን ኣዎንታዊ እንዲሆን ይፈልጋል። ለመዘጋጀት፡ ከልጆት ክትባት በፊት እና በኋላ ምን እንጠብቅ የሚለውን ይመልከቱ።

የበለጠ መረጋጋት፡ በራስ መተማመን፡ እና የፍራቻ መቀነስ እንዲኖራቸው ካርድ ሲስተም መጠቀም ይችላሉ።

ስለ ካርድ ሲስተም እዚ ውስጥ በመግባት ይማሩ CARD system እንዲሁም ስለ ካርድ ቸክሊስት

የ **CARD** [ካርድ] ትርጉም ይህ ነው፡

- C **Comfort [ምቹነት]**– የሚወዱት መጫወቻ ማምጣት፡ ምቹ ሹራብ መልበስ ወይም መክሰስ ኣስቀድሞ መውሰድ
- A **Ask [መጠየቅ]** – ልጆቻቹ ሊፈጠር ስለሚችለው ነገር ጥያቄ እንዲጠይቁ ማበረታታት
- R **Relax [መረጋጋት]** – በጥልቀት የመተንፈስ እና የመረጋጋት ሃሳብ በጋራ መለማመድ
- D **Distract [ኣተኩሮ መውሰድ]** – እቃ በመጠቀም፡ በማንበብ እና ከጓደኛ ጋር በማውራት ሃሳባቸው እዛ ላይ ብቻ እንዳይሆን ማድረግ

# ክትባት ኤችፒቪ
## ከ ካንሰር ይከላከላል

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
*Stay Well.*

ክትባት ኤችፒቪ -9 ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 አስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል በነጻ ይሰጣል።

## የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

ኣብዛኞቹ ሰዎች በሂወት ዘመናቸው ከ ሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ ንክኪ ይኖራቸዋል። ክትባት ኤችፒቪ ከ 9 የተለመዱ ከፍተኛ ኣደጋ ሊያስከትሉ ከሚችሉ የ ኤችፒቪ ኣይነቶች ይከላከላል።

- የጭንቅላት እና የኣንገት ካንሰር
- የማህጸን በር ካንሰር እና የሴት ብልት ካንሰር
- የፊንጢጣ ካንሰር
- የወንድ ብልት ካንሰር
- የብልት ኪንታሮት

## 3 ክትባት ኤችፒቪ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

ኣንድ ሙሉ በተከታታይ የተወሰደ ክትባት ኤችፒቪ፡ ታች ከተገለጹ በሽታዎች ይከላከላል፡

- ከ 90%% በላይ የ ማህጸን በር ካንሰር እና የ ብልት ኪንታሮት
- ኣብዛኞቹ የ ፊንጢጣ፡ የሴት ብልት፡ የሴት ብልት የ ውጭ ክፍል፡ የወንድ ብልት፡ የኣፍ እና የጎሮሮ ካንሰሮች

### ኣስተማማኝ ነው!

በ ዓለም ዙርያ ያሉት በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ኤችፒቪ ክትባትን በ ኣስተማማኝ መንገድ ወስደዉታል። ጎንዮች ጉዳቶች ኣብዛኛው ጊዜ ቀለል ያሉ ናቸው፡ ኣስተማማኝነቱ ደሞ በተከታታይ ክትትል ይደረግለታል።

### ቀላል ነው!

ነርስ ክትባት ኤችፒቪ ለመስጠት ወደ ልጆቻቹ ትምህርት ቤት ይመጣሉ- ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። የፍቃድ ቅጹን ብቻ በቀላሉ ሙሉት።

## የ ኤችፒቪ ክትባት ጥቅሞች

1. ከ ካንሰር ይከላከላል
2. ከ ተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል
3. እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው
4. ከ ብልት ኪንታሮት ይከላከላል
5. ለረዥም ጊዜ ይከላከላል
6. ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገለት ነው



### የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ እዚ ውስጥ ይግቡ**
**wdgpublichealth.ca/Gr7Consent**

ይሄን ቅረጹት

### ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**
**wdgpublichealth.ca/HPVfacts**

# የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት

## ከ ጉበት ኢንፈክሽን ይከላከላል

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
Stay Well.

‘የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 አስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉት በነጻ ይሰጣል።

## የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ከ ጉበት በሽታ ‘ቢ’ ቫይረስ ይከላከላል። ይሄ ቫይረስ የጉበት ጉዳት፡ የጉበት ካንሰር እንዲሁም ሞት ልያስከትል ይችላል። ‘ቢ’ ኣይነት የጉበት በሽታ በዋነኝነት የ ጉበት ካንሰር በ ካናዳ ያስከትላል።

## 3 ትምህርት ቤት ውስጥ የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

በጉበት በሽታ ‘ቢ’ ከተያዙት 10 ሰዎች መሃል ኣንዱ በሂወት ዘመኑ ሙሉ በሽታዉን ይሸከመዋል። ክትባቱን መውሰድ፡ በጊዜ ሂደት ሊመጡ የሚችሉ የ ጤና ኣደጋዎችን ለማስወገድ የበለጠ መንገድ ነው። የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት በጣም ውጤታማ ነው። በትክክለኛው መጠን ከተሰጠ 98% ሰዎችን ይከላከልላቸዋል።

### ኣስተማማኝ ነው!

የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት በጥንቃቄ መርመራ የተደረገለት ሆኖ ኣስተማማኝነቱም በተከታታይ ክትትል ተደርጎለታል። የሚያስከትለው የሰውነት ቁጣ ኣብዛኛው ጊዜ ቀለል ያለ ነው። ልጆቻቹ በ ጉበት በሽታ ‘ቢ’ ከሚያዙ ክትባቱን ቢወስዱ ኣስተማማኝ ይሆናል።

### ቀላል ነው!

ነርስ የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ለመስጠት ወደ ልጆቻቹ ትምህርት ቤት ይመጣሉ- ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። በቀላሉ የ ፍቃድ ቅጹን ብቻ ይሙሉት።

## የጉበት በሽታ ‘ቢ’ ክትባት ጥቅሞች



1. ከጉበት በሽታዎች እና ከጉበት ካንሰር ይከላከላል
2. ከተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል
3. እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው
4. ለረዥም ግዜ ይከላከላል
5. ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገለት ነው

### የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ እዚ ውስጥ ይግቡ**
wdgpublichealth.ca/Gr7Consent

### ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**
wdgpublichealth.ca/HepBfacts

ይሄን ቅረጹት

# ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት-ኤሲዋይዳብሊው

## ከ መኒንጎኮካል በሽታዎች ይከላከላል

PublicHealth
WELLINGTON-DUFFERIN-GUELPH
*Stay Well.*

**ይህ ክትባት ለሁሉ ተማሪ፡ ከሁሉ ጾታ እና ከ12 አስከ 13 ዕድሜ ላሉ ይሰጣል። በመጀመርያዎች ዕድሜ፡ ከተጋላጭነት በፊት እና የበሽታ መከላከል ኣቅም ሃያል በሚሆንበት ግዜ ከተሰጠ የበለተ ውጤታማ ይሆናል። ይሄ ክትባት ለሁሉ ተማሪ እስከ 12ኛ ክፍል በነጻ ይሰጣል።**

### የዚ ክትባት ስራ ምንድነው?

ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት ልጆትን ከ መኒንጎኮካል በሽታዎች ይከላከላል፡ ይህ ለሂወት በሚያሰጋ የ ባክተርያ ኢንፈክሽን የሚመጣ ሆኖ፡ መስማት መሳን፡ እንፍርፍሪት፡ የኣንጎል ጉዳት፡ የ እግሮች መጉደል እንዲሁም ሞት ልያስከትል ይችላል።

## 3 ትምህርት ቤት ውስጥ ይሄ ክትባት የሚወሰድበት ምክንያቶች

### ይሰራል!

ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት- ኤሲዋይዳብሊው መኒንጎኮካል በሽታዎች ለመከላከል ከ 80-85% ውጤታማ ነው። በሽታው በቀላሉ በ ሳል፡ ማስነጠስ፡ ወይም ኣብሮ በመብላት እና መጠጣት ይተላለፋል። በዚ በሽታ ከታመሙት 100 ሰዎች ኣንዱ በሂወት ኣይቀጥልም።

### ኣስተማማኝ ነው!

ይህ ክትባት በጥንቃቄ መርመራ የተደረገለት እና ኣስተማማኝነቱም በተከታታይ ክትትል ተደርጎለታል። የሚያስከትለው የሰውነት ቁጣ ቀለል ያለ ነው። ልጆቻቹ በ መኒንጎኮካል በሽታ ከሚያዙ ክትባቱን ቢወስዱ ኣስተማማኝ ይሆናል።

### ቀላል ነው!

ነርስ ክትባት መኒንጎኮካል ኮንጁጌት-ኤሲዋይዳብሊው ለመስጠት ወደ ልጆት ትምህርት ቤት ይመጣሉ—ቀጠሮ ማስያዝ ይሁን ዕረፍት መውሰድ ኣያስፈልግም። የ ፍቃድ ቅጹን ብቻ በቀላሉ ይሙሉት።

### የ ክትባት መኒንጎኮካል ጥቅሞች

1. **ከባድ ከሆነ ኢንፈክሽን ይከላከላል**
2. **ከተጋላጭነት በፊት ከተሰጠ የበለጠ ይሰራል**
3. **እስከ መጨረሻ 12ኛ ክፍል በነጻ ነው**
4. **ለረዥም ጊዜ ይከላከላል**
5. **ኣስተማማኝ እና ጥሩ ጥናት የተደረገላት ነው**



### የፍቃድ ቅጹን ለመሙላት ዝግጁ ናቹ?

**ኪው ኣር ኮዱን ቅረጹት ወይ በዚ ይግቡ**
**wdgpublichealth.ca/Gr7Consent**

### ለሚኖራቹ ጥያቄዎች

**1-800-265-7293 ተጨማሪ ቁጥር 7006**
**wdgpublichealth.ca/MenCfacts**

**ይሄን ቅረጹት**